# የመጽሐፍ ግምገማ

ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ፣*እመጓ*፡ ሰኔ 2007 ዓ.ም.፣ የገጽ ብዛት፡ 204

አንተነህ አወቀ[1]

**መግቢያ**

ድርሰቱ ልቦለድ (ከመጽሐፉ ጀርባ ሥነጽሑፍ ከመነሳቱ በስተቀር) ወይም የራስ የህይወት ገጠመኝ ስለመሆኑ በመግቢያውም ሆነ በድርሰቱ ውስጥ የተሰጠ ፍንጭ የለም። በእርግጥ በመጽሐፉ የጀርባ ሽፋን ስለደራሲው የሥነምህዳር ባለሙያና በመስኩ ተመራማሪ መሆን የተሰጠውን መግለጫ እና በድርሰቱ ውስጥ በዋና ገጸባህሪ ከተሳለው ሲሳይ ሙያና ልምድ ጋር በማገናዘብ የደራሲውን ገጠመኝ መሰረት ያደረገ ሥነጽሑፍ ነው ማለት ይቻል ይሆናል።

የእመጓ ልቦለድ ታሪክ ሚታዊ ገጽታ የተላበሰ ነው። ሲሳይ በዓለማዊ ህይወቱ ሳለ ከመንፈሳዊ አባቶች (እማሆይ እሴተ ማሪያምና አባ መርሐ ጽድቅ) ‹‹ታመሐል፣ ታመሐል እኛ የገዳም አባቶችህ መድሃኒቱ አለን እና ሳይበረታብህ ሳትውል ሳታድር ብቅ በል›› የሚል ግራ የሚያጋባ ጥሪ ይደርሰዋል። ጥሪውን ለመቀበል ሲያመነታ ይቆያል። ኋላም የጥሪውን ምንነት ለመረዳት ጥሪውን ያደረጉለት አባቶች ወዳሉበት ከዳንግላ 24 ኪሎሜትር ራቅ ብሎ ወደሚገኘው ፈለገ ብርሀን ደብረ ሃራ ማሪያም ገዳም ያደርጋል። ገዳማውያኑን ያገኛቸዋል። ተቀብለው ቢያስተናግዱትም የጥሪውን ምንነት በውል ሳይነግሩት ወደፊት እንጂ ወደኋላ መመለስ እንደሌለበት ይነግሩታል። የበለጠ ግራ ይጋባል። ይህ እንግዲህ በሚታዊ ጉዞ የመጀመሪያውን ቅጽር መዝለቅና መፈተን ነው።

በመመለስ ላይ ሳለ ወደገዳሙ ሲሄድ የመኪና መግቢያ መንገድ ያመላከቱት ሰው ትናንት ያለፈበትን መንገድ ታርሷል በሚል ሰበብ ይከልክሉታል። በሌላ መንገድ እንዲያልፍም ይነግሩታል። ከመኪናው ወርዶ ባመላከቱት በኩል አካባቢውን በተስፋ መቁረጥ ሲቃኝ ማገዶ ሲለቅሙ ያገኛቸው ሴት መነኮሳይያት ‹‹የደብረ አሮን መንገድ እኮ በዚህ አይደለም›› ይሉታል። እኔ የደብረ አሮንን መንገድ አይደለም የምፈልገው ወደ ዳንግላ ከዚያ ወደ ባህር ዳር የሚያደርሰኝን ነው›› ሲላቸው ‹‹ባህር ዳርም ደብረ አሮንም መንገዱ ያውም አይደል ብለው

[1] **አንተነህ አወቀ** በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ተባባሪ ፕሮፌሰር ነው።
**ኢሜል**፤ awekeewnetu@gmail.com

ወደመጣበት አቅጣጫ ያመለክቱታል፡፡ አብረዋቸው የነበሩት መነኩሲትም ‹‹ እ.. ደብረ አሮን መሄድህ አይቀርም ብለው ነው›› ይሉታል፡፡ ተደናግሮ በዛ በኩልማ ገበሬው እንደከለከለው ሲነግራቸው ‹‹ግድ የለም ተመልሰህ ሂድና ሩቅ መንገደኛ ነው ብለውሃል ቆለኛዋ እማሆይ በለው›› ይሉታል (57-58)፡፡ እንደተባለው ሲያደርግ ሰውየው ‹‹ብዙ ነገር ለማወቅ ትሞክራለህ የማለፊያህን ትንሽ ነገር ግን ማስታወስ ካቃተህ ጉዞህ ሳይከብድብህ አይቀርም፡፡ ነገርህ ሁሉ ግርድፍ አይሁን በል ና እለፍ› ይሉታል›› (60)፡፡ ከአካባቢው ራቅ እንዳለ ቆለኛዋ እማሆይና መንገድ የከለከሉት አባት ያደረጉትን አስታውሶ የሆነ የተቀናበረ ነገር መኖሩን ይገምታል፡፡ የገዳሙ አባት አባ መርሐ ጽድቅ ‹‹ዕርፍ ይዞ ወደ ኋላ የሚል የለምና በርታ›› እና ‹‹ወደ አቡነ አሮን የሚወስደው መንገድ…›› ያሉትን በማስታወስ ስልታዊ ጥቆማ እንደተደረገለት ይገምታል፡፡ ይህን በልቡ ይዞ ከቀናት በኋላ ከበህር ዳር ወደ ወሎ መቄት ደብረ አሮን ገዳም ይጓዛል፡፡ ጉዞው ወደተራራማ ስፍራ ነው፡፡ የበርካታ ሚታዊ ተረኮች ጉዞም በተመሳሳይ ወደተራራ ነው፡፡ ተራራ በሃይማኖታዊ ትረካዎች ተገቢ ስፍራ አለው፡፡ እግዚአብሄር ለኢየሱስ ደቀመዛሙርት የተገለጠላቸው በደብረ ታቦር ተራራ ላይ ነው፡፡ ሰይጣን ክርስቶስን የፈተነው ከተራራው ላይ ነው፡፡ ሌሎችም ሃማኖታዊ ተረኮች ይህንኑ ይገልጻሉ፡፡

የሲሳይ ወደ አቡነ አሮን ጉዞ ቀላል አልነበረም፣ አንደኛ ከዓለማዊ ኑሮው ተለይቷል፤ ከመንደሩ ርቆ ሄዷል፡፡ ጉዞው በበረሀ፣ በተራራ ላይ፣ በዋሻና በጨለማ ውስጥ ነው፡፡ የሰው አጽም፣ ተሳቢ እንስሳት ያጋጥሙታል፤ያስደነግጡታል፤ በፍርሃት ይርዳል፡፡ ሆኖም የሚያበረታው ሃይል አለው፡፡ በአቡነ አሮን ገዳም ከአባ አድሪል አስከሬን ሳጥን ላይ ‹‹ለከሳዋ በኮሳ›› ‹‹ውስተ ከርሠ እመ እጓል ሐቃላዊት ይሄሉ›› የሚል ለፍለጋው ፍንጭ የሚሆነውን ጽሑፍ ያገኛል፡፡ ስለአባ አድሪል ማንነትም በገዳሙ አባት አባ ተወልደ መድኅን ይነገረዋል፡፡ ወደ ባህርዳር ተመልሶ የሀረጉን ትርጉም ለማግኘት ሊቅ ይጠይቃል፡፡ ሆኖም ‹‹ለከሳዋ በኮሳ›› የሚለው ቃል ግዕዝ አለመሆኑን ይረዳል፡፡ ቃሉ ከጥንታዊ ቋንቋዎች ምናልባትም የአራማይክ እንደሆነ ይገምታል፡፡ ስለዚህ በወዳጁ በዶ/ር ሻሮን ሎውማን አማካኝነት የሥነመለኮትና የጥንት ቋንቋዎች ተመራማሪ የሆኑትን አሜሪካዊ ፕሮፌሰር ዴቪድ ራምስፊልድን ለማግኘት ጉዞውን ወደ አሜሪካ ያደርጋል፡፡ ከፕሮፌሰሩ ጋር ውይይት ካደረገ በኋላ የሚፈልገውን ነገር ያውቃል፤ ግን የት መፈለግ እንዳለበት ግራ ይጋባል፡፡ ሆኖም እያደር ፍንጭ እየተገለጸለት ጉዞውን ወደ ሰሜን ሸዋ እመጓ ቆላ ኡራኤል እና አርባሃራ መድሃኔዓለም ገዳማት ያደርጋል፡፡

*ሰሜን ሸዋ በገዳማቱ ዙሪያ እልህ አስጨራሽ እርምጃ በተራመደ ቁጥር ፍንጭ ያገኛል፡፡ አማሆይ ዕሴተ ማሪያም አባ አክሊሉን የመሰሉ ረዳቶችን ያገኛል፡፡ እነሱም ቢሆኑ የሚፈልገው ጽዋ መኖሩን እንጂ የት እንዳለ አይነግሩትም፡፡ እንዲያውም ፍለጋውን እንዲያቆምና መኖሩን ብቻ አምኖ እንዲቀበል እማሆይ ዕሴተ ይወተውቱታል፡፡ እሱ ግን እልህ ውስጥ ይገባል፡፡ በመጨረሻም ከተከለለው ቅጽር ይደርሳል፡፡ የቅጽሩን ኬላ ተሻግሮ፣ የገዘፈውን ጨለማ አሸንፎ፣መሰናክሉን ተራራና አዘቅቱን አልፎ፣ ከቅዱሱ ጽዋ መገኛ ቅጽር ይደርሳል፡፡ የቅዱሱን ጽዋ ጠባቂ ቅዱሳን አባቶች አልፎ ከቅዱሱ ጽዋ ይደርሳል፡፡ ሆኖም በሞትም ይሁን በህይወት በረከትን ይዞ መመለስ ሲገባው ስጋዊ ፍላጎቱ በማየሉ በተሳሳተ መንገድ ቀርቦ በቅዱሱ ጽዋ ታምራዊ ሃይል ይመታል፡፡ ራሱን ይስታል፡፡ ራሱን የሚያውቀው ከቀናት በኋላ ነው፡፡*

## *የሚት መገለጫዎች በአመጓ*

*ሲሳይ እንደሚታዊ ገጸሰብ ሁሉ ከዓለማዊ ኑሮው ሳለ ከቅዱሳን አባቶች ጥሪ ደርሶታል፡፡ ቢያመነታም ጥሪውን ተቀብሎ የተለያዩ ጉዞዎችን አድርጓል፡፡ ጉዞ ከላይ እንዳየነው የሚት ባህሪ ነው፡፡ እንደሚታዊ ተረክ ሁሉ ጉዞው አልጋ ባልጋ አይደለም፡፡ መደናገር ይበዛዋል፣ ትዕግስትን ይጠይቃል፤ በአስቸጋሪ የተፈጥሮ መልካምድር፣ በጨለማ ውስጥ ጉዞ አድርጎ የሚፈልገውን ጉዳይ የሚያመላክተው ፍንጭ ያገኛል፡፡ በጉዞው ደብረ ሃራ ማሪያምም ሆነ ደብረ አሮን የሚረዳው አካል ያገኛል፡፡ ይህም የሚታዊ ተረክ ባህሪ ነው፡፡ ከዋሽንግተን መልስ ምን እንደሚፈልግ ያውቃል፤ በትጋት ፍለጋውን ይጀምራል፡፡ ፍለጋ ከሚታዊ ተረክ ጭብጦች ውስጥ ዋነኛው ነው፡፡ በፍለጋው መንዝ እመጓ ቆላና አርባሃራ መድሃኔዓለም እማሆይ ዕሴተ ማሪያምንና አባ አክሊሉን ያገኛል፡፡ እንደ ሚቱ ሁሉ ተራዳኢያን ናቸው፡፡ ከብዙ እንግልት በኋላ ቅዱሱ ጽዋ የሚገኝበት ስፍራ ድረስ ዘልቆ ከጽዋው ከጠባቂ አባቶች ተደብቆ ቅዱሱን ጽዋ ያለበት ስፍራ ይደርሳል፡፡ የተጠበቀ ስፍራ፣ ጠባቂዎቸ መኖራቸውም የሚት ባህሪ ነው፡፡*

*በእማሬው ስንመለከተው ሲሳይ በአንድ በኩል የጽዋውን መኖር በማረጋገጥ ሚናውን ተወጥቷልና የተሳካለት ተጋዳላይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን አጨራረሱ ከመንፈሳዊው በማፈንገጡ ምክንያት (እንደሌባ ተደብቆ በመግባቱና ቅርስነቱ ያጓጓው በመሆኑ) ፍለጋው ጨንግፏል፤ ከበረከት ተለይቷል፤ ስለዚህ ያልተሳካለት ተጋዳላይ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ብዙውን ጊዜ የብሉይ ሚት ጀግኖች በድል ቢጨርሱም አልፎ አልፎ መጨንገፍ* (the fall) *ሌላው የሚት መገለጫ ጭብጥ ነውና ሲሳይም ከበረከቱ ሳይቋደስ ሲቀር እናያለን፡፡ታሪኩን በተምሳሌትም*

ከተረዳነው (ተምሳሌት ሌላው የሚት አብይ መገለጫ ነው) የጽዋውን መኖር በመረዳቱ ፈሪሃ እግዚአብሄር ሊያድርበት ቢችልም ደሙን ጠጥቶ ለመፈወስ እንዳይችል እንኳ ዳግመኛ ጽዋውን ማየት እንደማይፈልግ ነው ለአባ አክሊሉ የገለጸው፡፡

የሚቱ መሰረት በልቦለዱ አውድ ቅዱሱ ጽዋ/ቅዱሱ ኪዳን መንዝ፣እመጓ ቆላ የሚባለው ገዳም አካባቢ ዋሻ ውስጥ ይገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡ አባቶቹ ለቅዱሱ ጽዋ አመጓ ቆላ መገኘት ሁለት አይነት መግለጫዎችን ያቀርባሉ፡፡ የመጀመሪያውና በስፋት የሚታመንበት ከቅዱስ ኡራኤል መልአክ ጋር ተያይዞ የሚነገረው ሲሆን ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ ለንጊኖስ የሚባል ሰው ጎኑን በጦር ወጋው፤ቅዱስ ኡራኤል ከጎኑ የፈሰሰውን ደም በብርሀን ጽዋ ተቀብሎ ዓለምን በአራቱም ማዕዘን ረጨ፤ ከዚህ በኋላ መልአኩ የብርሃኑን ጽዋ በቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ በማዕከላዊ ምድር እመጓ ቆላ ተራሮች ውስጥ እስከ ዓለም ፍጻሜ አኖረው የሚል ነው፡፡ ከዚህ ታሪክ ጋር በተያያዘም መንዝ ደሙ የተረጨበት ምድር ማለት ነው፡፡

ሁለተኛው ከአርማትያሱ ዮሴፍና ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ጋር ተያይዞ የሚነገረው ነው፡፡ ክርስቶስ በተወለደ በ34ኛው ዓመት የኢትዮጵያ ንግሥት ጃንደረባ የነበረው ሰው ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ተጉዞ ሳለ ነገረክርስቶስን በመማሩ ራሱን ለክርስቲያናዊ ተልእኮ ለማስገዛት ከስልጣን እንዲሰናበት ይጠይቃል፡፡ ንግስቲቱ ጥያቄውን ተቀብላ ወደ እየሩሳሌም ሄደህ ለሀገራችን በረከት፣ ለሕዝባችን ምስክር የሚሆን ክርስቶስ የመወለዱ፣ የማስተማሩ የመሞቱና የመነሳቱ ምልክት የሚሆን አንዳች ነገር ይዘህ ተመለስ ትለዋለች፡፡ ጃንደረባው ወደ ኢየሩሳሌም፣ ኬብሮንና ሶሪያ ተጉዞ የአርማትያሱን ዮሴፍ አግኝቶ ታቦተ ጽዮንን በእምነትና በምሥጢር ጠብቃ ከምትኖር አገር መምጣቱን ገልጾ ለአምስት አመታት ሲያገለግለው ከቆዬ በኋላ የንግስቲቷን ሃሳብ ነግሮት ይህንን የከበረ ቅዱስ ቅርስ ለሕዝብህ የእምነት ውጤት የጸጋ ምልአት የሓዲስ ኪዳን ምስክር ይሆን ዘንድ ወደ ሀገርህ ይዘህ እንድትሄድ የእግዚአብሄር ፈቃዱ ሆኗል ብሎ ይሰጠዋል፡፡ ወደ ኢትዮጵያም ይዞ መጥቶ በጣና ሀይቅ ዳርቻ ሲኖር አባቶች ጉባኤ አድርገው ጌራ፣ ላሎና ማማ በተባሉ በሶስት ወንድማማቾች አዝማችነት ወደ መንዝ ምድር ይዘውት በመሄድ እመጓ ተራሮች ውስጥ ያስቀምጡታል፡፡ በመንዝ ላሎ ምድር፣ ማማ ምድርና ጌራ ምድር ተብለው የሚጠሩት ስፍራዎችም ከእነዚሁ ሶስት ወንድማማቾች ስምና ከሰፈሩበት ስፍራ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ልቦለዱ ይገልጻል፡፡

በዚህ ረገድ ይህን ትችት አቅራቢ የቅዱሳን ጽዋ ኢትዮጵያ ውስጥ መንዝ ስለመገኘቱ ንባብ ለማድረግና ሊቃውንትን ለማናገር ሞክሮ በድርሳነ ኡራኤል ውስጥ ኡራኤል መልዓክ ደሙን ስለመረጨቱ ከተገለጸውና በልቦለዱ ውስጥ የተገለጹት ስፍራዎች፣ ገዳማት፣ ባህላዊ ክንዋኔዎች እውነትነት በስተቀር ጽዋው ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖራል ተብሎ ስለመታመኑ መረጃ አላገኘም፡፡ ስለዚህ በልቦለዱ ታሪክ የጽዋው መንዝ መገኘትና የሲሳይ ቅዱሱን ጽዋ መፈለግ በእማሬው ፈጠራ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከሚትም አንጻር ካየነው በአፈታሪክ ከመታመኑ ውጭ ማረጋገጫ ሊገኝለት የማይችል ነገር ነው፡፡ በፍካሬው ካየነው ግን ድህነትን ፍለጋ ነው፡፡ ሲሳይ የደረሰው ጥሪ ቁስ እንዲፈልግ ሳይሆን መንፈሳዊ ጥሪ ነው፡፡ ክርስቶስን እንዲፈልግ፣ የክርስቶስን ስጋ በልቶ ደሙን ጠጥቶ እንዲፈወስ ነው፡፡

## የልቦለዱ ጭብጥ

ለሲሳይ የደረሰው ጥሪ ‹‹ታመሐል፣ ታመሐል እኛ የገዳም አባቶችህ መድሀኒቱ አለን እና ሳይበረታብህ ሳትውል ሳታድር ብቅ በል›› የሚል መንፈሳዊ ጥሪ ነው፡፡ ጥሪው የተጠነሰሰው በእማሆይ ዕሴተ እና በዳንግላው አባ መርሃ ጽድቅ ነው፡፡ የተጠራበት ምክንያት አርድዕቱን እንዲያግዝና በዚያውም በረከትን እንዲያገኝ ነበር፡፡ ጥሪውን ተቀብሎ ከገዳሙ የደረሰው ግን ጉባኤው ከተጠናቀቀና አባቶቹ ከተበተኑ በኋላ ነው፡፡ ሆኖም እማሆይ እሴተና አባ መርሃ ጽድቅ ተመካክረው አንዳንድ ምልክቶችን እየሰጡ ቅዱሱን ጽዋ በመፈለግ ረድኤት እንዲያገኝ በማሰብ ለታላቅ ተልዕኮ መንፈሱን አነሳስተውታል፡፡ የአርባሃራው መድኃኔዓለም አባ አክሊሉም ቢሆኑ ‹‹እውነት ነው የጠራንህ በረከትን በእምነት እንድትቀበል ወዲህም የትውልዱን ሕመም እንድታውቅ ነው፤ አንተ ደግሞ ሁሉን የማወቅ ጉጉትና ወረት የሚንጠው የዚህ ትውልድ ናሙና ነህና ትጠራና ትማር ዘንድ ይገባ ነበር›› (161) ይሉታል፡፡

በጥሪው መሰረት ገጸባህሪው ቅዱሱን ጽዋ ለማግኘት ጉዞውን ከገዳም ገዳም ያደርጋል፤ የሚፈልገውን ካወቀ በኋላ ደግሞ ጽዋው የት እንዳለ ለማወቅና ለማየት ከፍተኛ መንፈሳዊም ስጋዊም ጉጉት ያድርበታል፡፡ መንፈሳዊው ጉጉት ያደረበት ለክርስቶስ ካለው ፍቅር የተነሳ መሆኑን ይነግረናል፡፡ ችግሩ ግን ስጋዊው ፍላጎቱ አይሏል፡፡ ለዚህም ነው ‹‹በልዩ መግነጢሳዊ ኃይልህ ልቤን እየሳብክ በጉጉት የምታቀልጠው ክቡር ንዋይ ሆይ የት ይሆን ያረፍከው›› (112) ሲል የሚደመጠው፡፡ ቅዱስን ጽዋ አግኝቶ ስሙ እንዲጠራ፣ ለቤተክህነት፣ ለጳጳሱ፣ ለህዝብ፣ ለዓለም ሊያስተዋውቅ፣ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሊሰጥ ያስባል:: (183)

አካሄዱ ከመንፈሳዊው ማፈንገጡን ጠርጥረው የነበሩት እማሆይ እሴተማሪያም ‹‹በመንፈስ ጀምረህ በሥጋ ልትጨርስ ነው? ቅዱሱ የኪዳን ቅርስ የተሰወረው እኮ በመንፈስ ነው፡፡ በሥጋ ድካም የምታገኘው አይደለም›› (119) ብለውታል፡፡ በተጨማሪም ‹‹እንዳው ምናለበት ባትንከራተት፡፡ ቅዱሱ የኪዳን ቅርስ እንደሆነ እዚህ ለመኖሩ እርግጠኛ የሆንክ ይመስለኛል፤ ታዲያ ለምን ደስ ብሎህ በዚህ ረክተህ ወደ ቤትህ አትሄድም›› (184) ይሉታል፡፡ አካሄዱ ስጋዊ በመሆኑም ቅርሱ ከሚገኝበት ከቅዱሱ ተራራ መዋሉን ሲነግራቸውም እማሆይ ታላቅ ድንጋጤ ተሰምቷቸዋል (184)፡፡

ይህ በራሱ በልቦለዱ አንድ የዘመኑ ትውልድና የአባቶቻችን ልዩነት ነው፡፡ እነሱሳያዩ ያመኑ ብጽአን ናቸው የሚሉ ናቸው፡፡ በእምነት ብዙ ነገር ይሰራል፡፡ ሲሳይ ወኪል ሆኖ የቀረበለት የዘመኑ ትውልድ ግን በጥድፊያ የተሞላ ነው፡፡ ሳናይ አናምንም የሚል ተጠራጣሪ ትውልድ ነው፤ ሚስጥር አይጠብቅም፡፡ የልቦለዱ አንዱ ጭብጥ በእማሬው ይህን ይመስላል፡፡ በዚህ አንጻር ሲሳይ ለጥሪው ተገቢ ሰው ነበር ለማለት አያስደፍርም፡፡ ጥሪውን መቀበል የሚያስችለውም በቂ ዳራም በልቦለዱ አልቀረበም፡፡ በእርግጥ ሳያዩ ያመኑ ብጹአን ናቸው የሚለው ጭብጥ እውን የሚሆነው ሲሳይ እንዲህ አይነት ስጋዊ ፍላጎቱ ያመዘነበት ሰው ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ በፍካሬው ጥሪው ቁሱን ፈልጎ እንዲያገኝ ሳይሆን ተምሳሌታዊ ጉዞ በማድረግ ክርስቶስን፣ ድህነትን ዘላለማዊነትን እንዲያገኝ የታሰበ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ አቅጣጫ ጥሪው ተገቢ ቢመስልም ስጋዊውን መንገድ በመከተሉ ግን ፍለጋው አልሰመረለትም፡፡ በልቦለዱ ሌሎች ጭብጦችም በተቃርኖ ይነበባሉ፡፡ ሲሳይ ወደ አሜሪካ ሲሄድ አውሮፕላን ላይ ያገኛት በዲቪ አሜሪካ በስደት የምትሄድ ኢትዮጵያዊት ወጣት ፍንደቃ እና ዲስኩር፣ አሜሪካዊው ፒስኮር አንድሪስ ባርነር ለኢትዮጵያ ፍቅር እንዳለውና ረጅም የውጭ ሀገር ጉዞ ከማቆሙ በፊት ኢትዮጵያን ጎብኝቶ ሰላምና ዕረፍት ማግኘትን ከመመኘቱ ገለጻ ጋር ሲነጻጸሩ ለአንባቢው የሚሰጠው ትውልድን የመታዘብ አንዳች አይነት ቁም ነገር አለ፡፡

## የትረካ ስልት

ተረኩ የቀረበው በአንደኛ መደብ የትረካ አንጻር ነው፡፡ የትረካ አንጻር ታሪኩን ማን ነው የሚነግረን? ተራኪው ታሪኩን የሚነግረን የት ሆኖ ነው (የታሪኩ ተሳታፊ ወይስ ከውጭ ታዛቢ) ከአንባቢው ጋር ያለው ቅርበት እንዴት ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ይመልሳል፡፡

ታሪኩን የሚነግረን የታሪኩ ባለቤት የሆነው አቀንቃኙ ገጸ ባህሪ (ሲሳይ) ነው፤ በድርጊቱ ቀጥተኛ ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን ታሪኩ በሱ ዙሪያ የሚያጠነጥን ስለሆነ በመረጃ የበለጸገ ነው። ዋናው ታሪክ በአብዛኛው በመንገር ስልት የቀረበ ነው። በመንገር ስልት የቀረበ በመሆኑም ረጅሙ ታሪክ በ204 ገጽ አጥሮ ቀርቧል። ይህ ባይሆን ኑሮ የአንዱ ገዳም ጉዞና በገዳሙ ከመነኮሳቱ ጋር የሚደረገው መስተጋብር ብቻ ተስፋፍቶ በበርካታ ገጾች መገለጽ ይችል ነበር። በልቦለዱ ተራኪው አልፎ አልፎ ከአንባቢው ጋር ያለው ግንኙነት ቀጥተኛ ነው። ለምሳሌ

> ‹‹የአጥላው እናት እስኪ እሚጠጣ ነገር ፈልጊ›› እርሷም መልሳ ‹‹መጀመሪያ ትንሽ እህል ብትኸምስ አይሻልም›› ስለትለው ከሰማህ መንዝ ንግግሩም የፍቅር መሆኑን ተረዳ›› (90)

ሲል በቀጥታ ተራኪው (ሲሳይ) አንባቢውን በሁለተኛ መደብ ተባእት ጾታ አንተ ብሎ ያናግረዋል። ይህ አንባቢውን ለተራኪው ቅርበት እንዲሰማው ያደርገዋል። በእርግጥ የአንጻሩ መለወጥ ድንገተኛ በመሆኑ ደንገር ማድረጉ አይቀርም።

ከትረካ ስልት አንጻር የጊዜ አጠቃቀምን አስመልክቶ ታሪኩ በተራ የጊዜ ቅደም ተከተል ብቻ አይደለም የተተረከው። ምልሰት ተጠቅሟል። በምዕራፍ አንድ ታሪኩ የጀመረው ከመሀል ነው። ወደ አሜሪካ ሊሄድ ቦሌ አውሮፕላን ፍተሻ ላይ እያለ ነው። አሜሪካ የሚሄድበት ዋናው ምክንያት የአባቶችን ጥሪ ተቀብሎ ጥቂት ምእራፍ (ናዳ ማሪያምና አቡነ አሮን ገዳማት) ከተጓዘ በኋላ በተከታዮቹ ምእራፎች በምልሰት በሚነግረን በደብረ አሮን ገዳም በአባ አድሪል መቃብር ላይ ባገኘው እሱ የአርማናይት ቋንቋ ነው ብሎ በገመተው ጽሁፍ ‹‹ ለከሳዋ በኮሳ›› ምክንያት ነው።

መጽሀፉ አስራ ስምንት ምእራፎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያዎቹ አስር ምእራፎች መንፈሳዊውን ጥሪ የተቀበለው ‹ሲሳይ በስራና ከጥሪው ጋር ጋር በተያያዘ ወደ አሜሪካ ስላደረገው ጉዞና እዛም ከነገረ መለኮቱ ፕሮፌሰር ዴቪድ ጋር ባደረገው ውይይት ጥሪው ከቅዱሱ ጽዋ ጋር የተገናኘ መሆኑን ፍንጭ ስለማግኘቱ የተገለጸባቸው ናቸው። ይህ መረጃ ለአንባቢው በእግረ መንገድ የሚገለጸው ደግሞ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ከጎኑ ከተቀመጠው አሜሪካዊው ፒስኮር ሚስተር አንድሪያስ ጋር ባደረጉት ውይይት ነው። ምልሰቱ 5 ምእራፎችን ይዟል (ከምዕራፍ 5 — 9፣ ገጽ 36 — 77)። ምን እንደሚፈልግ አውቆ በአላማ መንቀሳቀስ የጀመረው ከምዕራፍ አስር በኋላ ባሉት ምዕራፎች ነው።

ደራሲው ምልሰት መጠቀሙ ጥሩ ቢሆንም እንደ ችግር ሊታይ የሚችለው የወንበር ተጋሪው ሚስተር አንድሪያስ በውይይቱ ያለው ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆንና የተረሳ መምሰል ነው፡፡ ሲሳይ በምልሰት ትረካውን ከጀመረ በኋላ አንድሪው 41 ገጽ ሙሉ በዝምታ ተውጦ ቆይቶ አስተያየት የሚሰጠው በገጽ 77 ነው፡፡ በአጭሩ የተረሳ ነው የሚመስለው፡፡አልፎ አልፎ ጣልቃ መግባት ነበረበት፡፡ ሲሳይ ታሪኩን አሳጥሮ ሊነግረው ሲገባም እያንዳንዷን ጥቃቅን ጉዳይ (በየመንገዱ የገጠመውን ሁሉ፤ ያሰበውን ሁሉ፣ ከታሪኩ ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌለውን ፣ተጫውቶት ያደገውን የልጆች ጨዋታ አይነቶችን ሁሉ) ነበር የሚገልጽለት፡፡ ስለዚህ ትረካው የአንድ ወገን ትረካ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ እንደምልሰቱ ሁሉ መጪውን ጠቋሚ ንግሮችም ያጋጥሙናል፡፡ ለምሳሌ በገጽ 27 ፕሮፌሰሩ፣

> እየፈለግኸው ያለው ነገር ከበድ ያለ መሆኑን እረዳለሁ፡፡ እንደዚህ ያሉ ጥንታዊና ሃይማኖታ ቅርሶች ብዙ ጊዜ ከምናውቀውና ከተለመደው እጅግ ወጣ ባለ ምሥጢራዊ ኃይል ይጠበቃሉ፡፡ አንዳንዴም ቅርሶቹም ራሳቸው ልዩ ኃይል ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በሃይማኖት ሰዎች ከሚሰጠው የመለኮታዊ ሃይል አምክንዮ ውጪ የፊዚክስ ምሁራን እንደነዚህ ያሉ ጥንታዊ ቅርሶች ራዲዮ አክቲቭ ከሆኑ ንጥረ ነገሮች በተሰሩ ሳጥኖች ወይም ቦርሳዎች ስለሚሸፈኑ ያለ ጥንቃቄ ወደነዚህ ቅርሶች መቅረብ በጨረር መጠቃትን ሊያስከትል ይችላል የሚል ትንታኔ ይሰጣሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ ወደነዚህ ምሥጢራዊ ቅርሶች መቅረብ የሕይወት ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል››(27)

ይሉታል፡፡ እንዳሉትም በመጽሀፉ ታሪክ መጨረሻ በሬዲዮ አክቲቭም ባይሆን በጽዋው ታምራዊ ሃይል ይመታል፡፡ ሲሳይ በፈለገ ብርሀን ናዳ ማሪያ ያገኘውም ገበሬ ቢሆን ገና ከጅምሩ ‹‹ብዙ ነገር ለማወቅ ትሞክራለህ የማለፊያህን ትንሽ ነገር ግን ማስታወስ ካቃተህ ጉዞህ ሳይከብድህ አይቀርም፡፡ (59) ይለዋል፡፡ እንዳለውም ጉዞው ከባድ ነበር፡፡ ሲሳይ ይህን ሰው ገበሬው ይበለው እንጂ ከንግግሩና ከስራው ሲሳይ የተጠራበትን ምክንያት የሚያውቅ የመነኮሳቱ አባል ነው የሚመስለው፡፡

## የገጸባህሪ አሳሳል

ገጸባህሪ አሳሳልን አስመልክቶ እንደ ሚታዊ ትርክቶች ሁሉ የእመን ገጸ ባህሪ መንፈሳዊው ጥሪ የሚደርሰው ለሰርክ ህይወቱ እየማሰነ እያለ ነው፡፡ ገጸባህሪው ሲሳይ በምልሰት እንደሚነግረን የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያ የነበረና እንደማናቸውም አለማዊ ሰው ለስጋው የሚያስፈልገውን ለሟሟላት ደፋ ቀና ሲል የነበረ ምናልባትም በታታሪነቱ ኑሮውን ለውጦ የተሻለ ኑሮ መኖር የጀመረ ሰው ነው፡፡

*ምናልባትም ‹‹ታመሐል›› መባሉ በመንፈሳዊው ህይወት እንዲጸና መታጨቱ ሊሆን ይችላል፡፡ መነኮሳቱ ደጋግመው እንደነገሩት ችኩልነት ስላለበት የጽዋውን መኖር ከማረጋገጥ ውጭ ጽዋውን በስርዓት ለማየት አልቻለም፡፡ በችኩልነቱና በራስ ወዳድነቱ ከመነኮሳቱ ተደብቆ ገልጦ ለማየትና ለመንካት በመሞከሩ በጽዋው ሃይል ተመቷል፡፡ ስለዚህ ከበሽታው ተፈውሷል ግቡን መቷል ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ የለም፡፡ አባ አክሊሉ በግልጽ እንደነገሩት እርሱ የዘመኑ ሰው ተምሳሌት ነው፤ እርጋታ የለውም፤ ራስ ወዳድነት ዝና የተጠናወተው ነው፡፡ ምስጢር የሚጠብቅ ሰውም አይደለም፤ ቢሆንልህ ትጽፈዋለህ እንዳሉት በእርግጥም ተራኪው እየተረከልን ነው፡፡ ከዚህና ‹‹ሳያዩ ያመኑ ብጹአን ናቸው›› ከሚለው ጭብጥ አንጻር አሳሳሉ ተገቢነት አለው፡፡*

*ከላይ በቀረቡት ገለጻዎች በሚታዊ ትረካ ስርዓት ተጋዳላዩ ከሰርካዊው ህይወቱ እንደሚታጭ እና ሲሳይ በዚህ መንገድ ለመንፈሳዊ ተግባር መታጨቱ ተገልጿል፡፡ ሆኖም ሲሳይ ለረድዕነት መታጨት የሚያስችለው የእምነቱን ጥንካሬ የሚገልጽ በቂ ዳራ አልተሰጠም፡፡ እማሆይ እሴተም ሲሳይን በረድዕነት ለማጨት የሚያበቃቸው ጠንካራ መንፈሳዊ ግንኙነት ከሲሳይ ጋር እንደነበራቸው የተሰጠ ዳራ የለም፡፡*

## *የመቼት ገለጻ*

*የመቼት ገለጻው የበለጸገ ነው፡፡ መልክአ ምድሩ፣ ዋሻዎቹ፣ ተራራው፣ በአጠቃላይ ሥነምህዳሩ በምናብ ለስሜት ህዋሳት ሊደርስ በሚችል መልኩ የተገለጹ ናቸው፡፡ ለገለጻው መሳካት የደራሲው የስነምህዳር ባለሙያ መሆንና ስለእምነቱ ያለው መረጃና የተጠቀሱትን ገዳማትና ቅርሶች ማወቁ አስተዋጽኦ ሳያደርግለት አልቀረም፡፡ ለምሳሌ በቅዱሱ ተራራ በደረሰ ጊዜ የዕጣነ ሞገሩን ሽታ ሳይቀር ነበር በምናብ የሚያስሸትተን፡፡ በተመሳሳይ ፓርኩን ሲያስጎበኘን የሳሩን ስፖንጃዊ ባህሪ የረገጥነው ያህል እንዲሰማን ነበር የሚያደርገን፡፡ ይህ ደግሞ ከቋንቋውም ብስለት ጭምር የመነጨ ነው፡፡ የገዳማቱን ቋንቋ ያውቀዋል፤ ስነስርዓቱን ያውቀዋል፡፡ ማወቅ ብቻ አይደለም ልማዱን፣ ባህሉን ሊያሳውቀን ሁሉ መግለጫ ይሰጠናል፡፡*

*በአጠቃላይ ድርሰቱ በይዘት ረገድ አነጋጋሪ ብቻ ሳይሆን ጥሩ አማራጭም ነው፡፡ በፍቅርና ወሲብ እንዲሁም ባዛና ህይወት ለተሰላቹ አንባቢያንም ትልቅ የምስራች ነው፡፡ በቅርጽም ረገድ ሚታዊ ልቦለድም በመጻፍ በዘርፉ ግምባር ቀደም ሊባል ከሚችሉት ሥራዎች ውስጥ ሊመደብ ይችላል፡፡ ከቋንቋ ገር በተያያዘ መጽሐፉ በጥንቃቄ የአርትኦት ስራ ተሰርቶበት ቢሆን ጥሩ ነበር፡፡ በየገጹ የፊደል ግድፈቶች አሉበት፡፡*